# የአሜሪካ መንግስት የትምህርት ክፍል

# የሰው ልጅ መብት ቢሮ፤

# እኩል የሆነ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ለመስጠት

U.S. Department of Education
Office for Civil Rights
Washington, DC 20202-1100

ተከለሰ ሴፕተምበር 2004

## የሰው ልጅ መብት ሕጎች ያስከተሏቸው ተጽዕኖ

ፌደራሉ የሰው ልጅ መብት ሕጎችን የማስተግበሩ ሂደት በየአሜሪካ የትምህርት አሰጣጥ ላይ ብዙ ለውጦችን ሲያመጣ፣ በሚልዮን የሚቆጠሩ ተማሪዎች ያላቸውን የትምህርት እድልንም አሻሽሏል። ግለሰቦች የሚፈልጉትን የትህምርት ዓይነትንና የስራ ዓይነትን በነጻነት እንዳይመርጡና ይከለክሏቸው የነበሩ አያሌ እንቅፋቶች አሁን ተወግደዋል። በአሁኑ ጊዜ ብዙ ትምህርት ቤቶች፣ እንግሊዝኛ በደንብ የማይችሉ ተማሪዎችን በየትህምርት ፕሮግራሞቻቸው ውስጥ ለመሳተፍ እንደሚችሉ አድርገውላቸዋል። ተጨማሪ ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች በአሁኑ ወቅት ሳፕሊመንታል እርዳታንና አገልግሎቶችን ተጠቅመው መደበኛ የትምህርት ክፍለ ጊዜ እየተከታተሉ ነው።

በተጨማሪም፣ ፌደራላዊውን የትምህርት ፕሮግራም በአጠቃላዩ ለማሻሻል ተብሎ የወጣው፣ ማንም ልጅ ወደ ኋላ እንዳይቀር የሚለው የ 2001 አዋጅ (No Child Left Behind Act of 2001) (NCLB) ቢሮው ያለውን፣ በመላው ሀገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ልጆች ሁሉ እኩል የትምህርት ዕድልን መስጠትንና እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ ትምህርት እንዲኖር መግፋትን የሚያደፋፍር ነው። የ NCLB አዋጅ፣ ለሁሉም ልጆች፣ በዘር፣ ብሔር፣ ጾታ፣ ስንክልና ወይም የማሕበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ምልክያት ልዩነት ሳይደረግ፣ በእኩል፣ ከፍተኛ ደረጃ ላለው የትምህርት እድል መስጠትን የሚያረጋግጥ፣ ግልጽ የሆኑ መመሪያዎችን ያዘለ ነው።

የሰው ልጅ መብት ሕጎች፣ የትምህርት ቤቶቻችንን፣ ክፍሎችን፣ አዳራሾችን፣ የስፖርት ሜዳዎችንና አሬናዎችን በሮች ከፍተውልናል። በዚህም ምክንያት፣ በአሁኑ ወቅት ባለችው አሜሪካ ውስጥ ያሉ፣ ከተለያዩ ቦታዎች የተሰባሰቡ ሰዎች፣ በንድግ፣ በመንግስት፣ በሳይንስ፣ በኢደ ጥበብና በትምህርት ዘርፎች ውስጥ፣ የነገ መሪዎች ለመሆን በዚህ በር እየገቡ ነው። የሰው መብት ሕጎች ከዚህ ከ NCLB አዋጅ ጋር በመሆን እነዚህ በሮች ለሁሉም ተከፍተው እንደሚቆዩ ያደርጋሉ።

## የሰው ልጅ መብቶች ቢሮ ሐላፊነቶች

በአሜሪካን የትምህርት ክፍል (U.S. Department of Education) (Department) ውስጥ የሚገኘው የሰው ልጅ መብቶች ቢሮ (Office for Civil Rights) (OCR) የፌደራል እርዳታ የሚያገኙ የትምህርት ተቋሞች የማዳላት ተግባርን እንዳይፈጽሙ ይረጋገጥ ዘንድ የፌደራል ሕጎችን የማስፈጸም ሓላፊነት የተሰጠው አካል ነው። OCR፣ በዘር፣ ቀለም፣ የትውልድ ሀገር፣ ጾታ፣ ስንክልናና እድሜ ምክንያት፣ ከቢሮው እርዳታ

በሚያገኙ ፕሮግራሞችና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ማዳላትን የሚቃወሙ የፌደራላዊ የሰው ልጅ መብት ሕጎችን ያስከብራል። የሰው ልጅ መብት ሕጎች፣ በሀገር ደረጃ በየትምህርት ፕሮግራሞች ወይም እንቅስቃሴዎች ውስጥ ማዳላትን ለማስወገድ የተገባውን ቃል ኪዳን ይወክላሉ። እነዚህ ሕጎች፤

- በ1964 የወጣው የሰው ልጅ መብቶች አንቀጽ 6 (በዘር፣ ቀለምና በድውልድ ሀገር የሚደረግ ማዳላትን ይቃወማል)።
- በ1972 የወጡት የትምህርት ሕግ መሻሻሎች አንቀጽ 9 (በጾታ ምክንያት ማዳላትን ይቃወማሉ)።
- በ1973 የወጣው የመልሶ ማቋቋም አዋጅ (Rehabilitation Act) ክፍል 504 (በስንክልና ምክንያት ማዳላትን ይቃወማል)።
- በ1975 የወጣው በእድሜ ምክንያት ማዳላትን አስመልክቶ የወጣው አዋጅ (በእድሚ ምክንያት ማዳላትን ይቃወማል)።
- በ1990 የወጣው አካለ ስንክልና ያላቸው አሜሪካውያንን በሚመለከት የወጣው አዋጅ (Americans with Disabilities Act) አንቀጽ 2 (እንደ የመንግስት ትምህርት ቤት ቀጠናዎች፣ የመንግስት ኮሌጆችና ቤተ መጻሕፍቶች በመሳሰሉ የህዝብ ተቋሞች ውስጥ የፌደራላዊ እርዳታ ቢያገኙም ባያገኙም፣ በአካለ ስንክልና ምክንያት ማዳላት እንዳይፈጸም ይቃወማል)።

በተጨማሪም፣ OCR በ2001 የወጣውን፣ ማንም ልጅ ወደ ኋላ አይቀርም (No Child Left Behind) የሚለው አዋጅ ክፍል የሆነው ን ወደ የአሜሪካን ሀገር ቦይ ስካውት እኩል የመግባት እድል የሚሰጠውን አዋጅ (Boy Scouts of America Equal Access Act) ያስተገብራል። በየአሜሪካን ሀገር ቦይ ስካውት እኩል የመግባት እድል አዋጅ ስር፣ ለማንኛውም አንድ ወይም ከአንድ ለሚበልጡ፣ የውጭ ወጣቶች ወይም የማሕበረሰብ ክፍሎች አገልግሎት የሚሰጥ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም የስቴት ወይም የአካባቢው የትምህርት ተቋም፣  ከትምህርት ሰዓታት ውጭ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ለመሰብሰብ ከፈለጉ፣ ለማንም ከአሜሪካ ቦይ ስካው ጋር ወይም በአሜሪካን ሀገር ሕገ መንግስት አንቀጽ 36 ላይ ከተጠቀሱት ቡድኖች ጋር ዝምድና ላለው ማንኛውም ቡድን እንደ ሀገር ወዳድ ዜጋ ማዳላትን መፈጸም የለበትም።

አብዛኛዎቹ የ OCR እንቅስቃሴዎች በምላው ሀገሪቱ ውስጥ ባሉ የማስፈጸሚያ ቢሮዎች ውስጥ ነው የሚፈጸሙት። በዋሺንግተን ዲሲ

ውስጥ የሰው ልጅ መብቶች ቢሮ ምክትል ዋና ጸሐፊ አጠቃላዩን አመራር እና ቅንብርን ይሰጣል።

ሕጎቹ የትምህርት ተቋሞችንም  ይመለከታሉ

አብዛኛዎቹ የትምህርት ተቋሞች ፌደራላዊ የገንዘብ እርዳታ ስለሚቀበሉ፣ የሰው ልጅ መብቶች በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹን የትምህርት ተቋሞች ይመለከታሉ። ይህም ማለት፣ የሰው ልጅ መብት ሕጎች ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ይሸፍናሉ፤

- ወደ 15,000 የሚሆኑ የትምህርት ቀጠናዎችን።
- ከ 4,100 በላይ ይሚሆኑ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች።
- እንደ የጭነት መንጃ መንዳት መለማመጃ ትምህርት ቤትና የኮስሚቲክስ ትምህርት ቤት የመሳሰሉ፣ ከአሶሼት ዲግሪ በታች የሚያስመርቁ፣ ወደ 5,000 አካባቢ የሚሆኑ ተቋሞች።
- እንደ ቤተ መጻሕፍት፣ ሙዚየም፣ የተግባረ እድ ማሰልጠኛና የእስር ቤት ተቋሞችን የመሳሰሉ በሺ የሚቆጠሩ ተቋሞች።

ሕጉ ተማሪዎችንና ሰራተኞችን ይመለከታል።

የሰው ልጅ መብቶቹ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን፣ ቁጥራቸው ብዙ የሆነውን በትምህርት ገበታ ላይ የሚገኙ ወይም ለመግባት ማመልከቻ የሞሉት ተማሪዎችን መብት የሚጠብቅ ነው፤

- በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ወደ 54.3 ሚልዮን የሚሆኑ ተማሪዎች።
- ኮሌጆቻውንና ዩኒቨርስቲዎቻችን ውስጥ የሚማሩ ወደ 16.4 ሚልዮን የሚሆኑ ተማሪዎች።

በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ፣ ሕጉ በትምህርት ተቋሞች ውስጥ የሚሰሩ ወይም ለመስራት የሚሞክሩ ሰዎችን መብት ይጠብቃል።

**OCR ከሰፊው ህዝብ ማዳላትን በሚመለከት ብሶቶችን ይሰማል።**

OCR ያለውን ሐላፊነት የሚወጣው፣ በተማሪዎች፣ ወላጆችና ሌሎች ለደረሱ ቅሬታዎች መፍትሔ በመፈለግ ነው። ብሶቱን የሚያቀርበው ግለሰብ ወይም ድርጅት የማዳላት ተግባር የተፈጸመበት ወገን የግድ የለበትም። ሌላ ግለሰብንው ወይም ቡድንን ወክሎ ብሶት ማሰማት ይችላል። በአጠቃላዩ፣ OCR እርምጃ የሚወስደው፣ የመጨረሻው የማዳላት ተግባር ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ በ180 ቀኖው ውስጥ ክስ ከተመሰረተና ከሳሹ በተከታታይ የሚፈጸም የማዳላት ፖሊሲ ወይም ተግባር እንዳለ ሲያሳውቅ ነው።

OCR ፣ በየዓመቱ በግምት 5000 ክሶችን ይቀበላል። ክሶቹም፣ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ዕድልን በሚመለከት ዓብይ ነጥቦችን ያዘሉ ናቸው።

በአንቀጽ 6 ስር — በዘር፣ ቀለምና የትውልድ ሀገር ምክንያት የሚፈጸሙ የማዳላት ተግባሮች — ክሶቹም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ነጥቦች ያጠቃልላሉ፤

- በዘር ወይም በብሔር እንዲሁም በችሎታ መከፋፈል።
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በሌላ ቋንቋዎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን የማግኘት ችሎታ።
- ስነስርዓትን የማስጠበቂያ እርምጃዎች።
- የተማሪዎች አመዳደብ ፖሊሲ። ለጎበዝ ተማሪዎች ተብሎ የተዘጋጀ የምደባ ፕሮግራሞችን ጨምሮ።
- ከቀጠና ወደ ቀጠና የሚደረጉ የተማሪ መዘዋወሮች።
- ትምህርት ቤቶችን ዲሰግሪጌት (desegregation) ማድረግ።
- በዘር ምክንያት የሚፈጸሙ ስቃዮች።
- በኮሌጅ ካምፓሶች ውስጥ የተማሪ መኖሪያ ቤቶች ድልደላ።
- አካዳሚያዊ ግሬድ አሰጣጥ።

በአንቀጽ 9 ስር — በጾታ ምክንያት የሚፈጸም የማዳላት ተግባር — የሚሰነዘሩት ክሶች እነዚህን ነጥቦች ያጠቃልላሉ፤

- ግብረ ስጋዊ ስቃይ።
- በትምህርት ቤቶችና በኮሌጆች ውስጥ በሚደረጉ የአትሌቲክ ተግባሮች ውስጥ እኩል ዕድልን ምስጠትን በሚመለከት።
- ያረገዙ ተማሪዎች የሚያገኙትን መስተንግዶ በተመለከተ።
- ድሕረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጡ ተቋሞች ያላቸው የተማሪ አቀባበል ፖሊሲ።

በክፍል 504 እና አንቀጽ 2 ስር — በአካለ ስንኩሎች ላይ የሚፈጸም የማዳላት ተግባር — የሚሰነዘሩት ክሶች እነዚህን ነጥቦች ያጠቃልላሉ፤

- ወደ የትምህርት ቤቱ ተቋሞችና ፕሮግራሞች ለመግባት ያላችወ ችሎታ።
- አስፈላጊ የሆኑ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች።
- ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች የሚያስፈልጋቸውን ተማሪውች የመገምገሚያና የማስተናገድ አገልግሎቶች።
- ተማሪውች ካላቸው የትምህርት ፍላጎቶች ጋር በሚዛመድ መንገድ ነጻነት በተሞላው አካባቢ ውስጥ ተማሪዎችን ማስተማር።
- የአካለ ስንክልና ያላቸውን ተማሪዎች ማስቆምንና ማባረርን።
- አካዳሚያዊ ለውጦችና መሻሻሎች።
- የስሜት ህዋሳቶቻቸር በደንብ ለማይሰሩ፣ በእጅ ነገሮችን የማድረግና የመናገር ችግር ላላቸው ተማሪዎች የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ቁሳቁሶች።

## OCR እንዴት አድርጎ ቅሬታዎችን እንደሚፈታ

ቅሬታዎችን በመፍታት ላይ የ OCR ቀዳማዊ አላማ፣ ከሳሽ ላቀረበው የማዳላት ተግባር ክስ፣ በቶሎ፣ ፍትሐዊና ተገቢ መፍትሔ ማግኘት ነው። OCR አንድን ችግር ለመፍታት የተሻለው መንገድ ከተማሪዎች፣ ወላጆች፣ የማሕበረ ሰብ ቡድኖች፣ ስቴትና በአካባቢው ከሚገኙ የትምህርት ኤጀንሲዎች፣ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ጋር በመተባበር መሆኑን ተገንዝቧል።

OCR ችግሮችን ለመፍታት፣ አስቀድሞ ቅሬታዎችን ሰምቶ እልባት ከመፈለግ ጀምሮ እስከ ከወገኖቹ ጋር ስምምነት ላይ ተደርሶ በፍላጎት እንዲታረሙ ምርመራ ማካሄድና መደራደር ድረስ፣ የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማል።

OCR፣ በፍላጎት እንደማይታረሙ ከወሰነ በኋላ ብቻ ነው፣ በአስተዳደር በኩል የሚካሄድ የአቤቱታ ስነስርዓት እንዲካሄድ ወይም ጉዳዩ ወደ የአሜሪካን መንግስት የፍትህ ቢሮ (U.S. Department of Justice) እንዲተላለፍና መፍትሔ እንዲገኝለት የሚያደርግ። ይህ ተለዋዋጭ መንገድ፣ OCR ከዚህ በታች ያሉትን ለማከናወን ያስችለዋል፤

- የአቤቱታው ስነስርዓት በሚጀመርበት ወቅት ላይ ወቅታዊና የሚሰራ መፍትሔ ማግኘት።
- የማዳላት ተግባርን የሚቃወሙ ሕጎች ተፈጻሚነታቸውን ለማረጋገጥ መስራት።
- ቅሬታዎችን በመፍታት ሂደት ላይ ተማሪዎች፣ ወላጆችና የትምህርት ቤቱ ባልደረባዎች ዋና ሚና እንደሚኖራቸው ማድረግ።

**OCR ሰው ምን ያህል ሕጎችን እንደሚከተል ለማወቅ ግምገማዎችን ያካሂዳል።**

በኤጀንሲው የሚነሱ ጉዳዮች፣ በዘልማት "ኮምፕላያንስ ረቪው" በመባል የሚታወቁ ሲሆኑ፣ አስቸጋሪ የሚመስሉ፣ በሀገር ደረጃ የሚታዩ ወይም አዲስ የመጡ ችግሮች ላይ በማተኮር ሕግን ካለመከተል ምክንያት በሚነሱ ችግሮች ላይ OCR እንዲያተኩር ያስችሉታል።

አላማ ያላቸው የኮምፕላያንስ ረቪው ግምገማዎች የ OCR አቅምን በአግባቡ ተጠቅሞ ከፍተኛውን ለውጥ ለማምጣትና የሕግ ማስከበር ፕሮግራሞችንም ደግሞ ሚዛናዊ የሆነ ድርሻ ይሰጣሉ። የኮምፕላያንስ ረቪው፣ ሕጉን በሚመለከት እምብዛም እውቀት የሌላቸው፣ እንደ እጅግ በጣም ድሆች ወይም እንግሊዝኛ የማይናገሩ ግለሰቦች፣ ያላቸውን የሰው ልጅ መብት መጠበቁን ያረጋግጣል። የ OCR ኤክስፔሪየንስ እንደሚያሳየው፣ ተጠንቅቆ የሚደረግ የኮምፕላያንስ ግምገማ፣ አብዛኛውን ጊዜ ተገልጋዩን የሚጠቅሙ የፖሊሲ ወይም የፕሮግራም ለውጦች እንደሚከሰቱ ያደርጋል። አቤቱታ በሚቀርብበት ወቅት ግን፣ ከሳሹን የሚጠቅሙ መፍትሔዎች ብቻ ነው የሚቀርቡት።

OCR ግምገማዎችን የሚመርጠው፣ በከሳሾቹ የቀረቡ አቤቱታዎችን፣ መረጃዎችን፣ የትምህርት ቤት ቡድኖች፣ የዜና ማሰራጫዎችና ህዝብን ጨምሮ፣ ከተለያዩ ምንጮች ካገኛቸው መረጃዎች ነው የኮምፕላያንስ ግምገማውን የሚመርጠው። OCR ከዚህ በታች ባሉ ጉዳዮች ላይ የኮምፕላያንስ ግምገማ አካሂዷል፤

- ❖ በስፔሻል የትምህርት አይነትና ሎው ትራክ (low-track) ኮርሶችን በሚከታተሉ ማይኖሪቲ (minority) ተማሪዎች።
- ❖ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች፣ የትምህርት ቤቱ ቀጠና ያለውን ሌሎች የእንግሊዝኛ ፕሮግራም አገልግሎቶችን የመጠቀም አቅም።
- ❖ ስንክልና ላላቸው ተማሪዎች ተገቢ የሆነ በነጻ የሚሰጥ የመንግስት ትምህርት።
- ❖ ማይኖሪቲ ተማሪዎች ስጦታ ላላቸውና ጎበዝ ለሆኑ የሚሰጡ ኮርሶችንና አድቫንስድ የሆኑ ኮርሶችን ለማግኘት ያላቸው እድል።
- ❖ በዘር ምክንያት የሚደርሱ ስቃዮች።
- ❖ ላልተፈለገ የግብረ ስጋዊ ተግባር የሚገፋፋ አካባቢ።
- ❖ በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ዲሴግሪጌሽን (desegregation) ማካሄድ።

OCR፣ ፌደራል፣ ስቴትና በአካባቢው የሚገኙ የትምህርት ኤጀንሲዎች፣ እንዲሁም ወላጆችና ሌሎች ሀላፊነት የሚሰማቸው ወገኖች፣ ለሁሉም እኩል የሆነ የትምህርት እድልና ጥቅም የመስጠት የጋራ አላማ እንዳላቸው ይገነዘባል። OCR፣ ያለውን ሞያ ከነዚህ ባለጋራውችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር ሆኖ፣ ሊሰሩ የሚችሉ፣ ሁሉም ተማሪዎች ወደ የትምህርት ገበታ ለመሳተፍ ያላቸውን ዕድል ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ መፍትሔዎችን ጨምሮ፣ ሊሰራ የሚችል መፍትሔን ለማግኘት ይሞክራል።

የ OCR ቴክኒካዊ እርዳታ ግለሰቦችንና ተቋሞችን ይረዳል።

የ OCR ቴክኒካዊ እርዳታ ጥረቶች የሰው ልጅ መብት ሕጎች እንዳይጣሱ መከላከል ነው። ይህም ሊፈጸም የሚችለው፣ እርዳታ ተቀባዮች ሕጉን እንዲከተሉ በመርዳትና ተጠቃሚዎች ያላቸውን መብቶች በማስረዳት ነው። በየሰው ልጅ መብቱ ከተጠበቁት በሚልዮን የሚቆጠሩ ተማሪዎች አንጻር ሲታይ፣ የ OCR ጥረት ብቻውን ሕገወጥ የሆነ በትምህርት ላይ የሚፈጸም ማዳላትን ሊከላከል እንደማይችል ይረዳል። ተማሪዎች፣ ወላጆችና አስተማሪዎች ሕገወጥ የሆነ የማዳላት ተግባር እንዳይፈጸም ለመከላከል የሚያስችል እውቀትና ዘዴ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

ለቅሬታዎች መፍትሔ በሚፈለግበት ሒደት ወይም በኮምፕላያንስ ግምገማ ወቅት ተቋሞች ሕግን መከተል እንዲችሉ OCR አስፈላጊውን እርዳታ ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም፣ OCR በቦታው ተገኝቶ ምክርን ምስጠት፣ ክፍል ውስጥ ስልጠናን መስጠት፣ ዎርክሾፖች፣ ስብሰባዎችና ኮንፈረንሶች ውስጥ በመሳተፍ በመሳሰሉ በተለያዩ መንገዶች ወቅታዊ የሆነ ቴክኒካል እርዳታ የሚሰጥበት ሰፊ የሆነ ፕሮግራም አለው። OCR፣ ከሌሎች ፌደራል ኤጀንሲዎች፣ የስቴትና በአካባቢው የሚገኙ የትምህርት ኤጀንሲዎች፣ የማሕበረሰብ ቡድኖች፣ ወላጆች፣ ተማሪዎችና ሰፊው ህዝብ እርሳታ ሲጠየቅ፣ እርዳታውን ይሰጣል።

አብዛኛዎቹ የ OCR ቢሮዎች፣ ለባለጋራዎቻችን፣ ለሚመለከታቸው ወገኖችና ከሰፊው ህዝብ ለተውጣጡ አባሎች በቶሎ መመለስ እንዲያስችል በመባል፣ የደንበኛ አገልግሎት ቡድን አቋቁመዋል። OCR የራሱ ሆምፔጅ አለው። http://www.ed.gov/ocr ። ይህ ዊብ ፔጅ ከዲፓርትመንቱ ዌብ ሳይት ጋር የተገናኘ ነው።

ለወደፊት ልንወጣቸው ያልብን ችግሮች

የሰው ልጅ መብት ሕጎችን በማስተግበር የታየውን መሻሻል መገንዘብ የሚቻል ቢሆንም፣ በሀገሪቱ ውስጥ አንዳንድ ሰዎች ሕገወጥ በሆነ መንገድ የተሟላ የትምህርት እድል እየተከለከሉ ነው። አካለ ስንኩልና ላላቸው፣ ለሴቶች፣ ለአረጋውያን አሜሪካኖችና በዘርና በቋንቋ አናሳ ለሆኑ የማሕበረሰቡ ክፍሎች ጠንቀር ያሉ ኮርሶች ወይም ፕሮግራሞች ናቸው ተብለው የሚገመቱ ፕሮግራሞችን የመከልከል ፖሊሲዎችና አሰራሮች እስካሁን ድረስ አሉ። የሰው ልጅ መብትን የማስከበሩ ፕሮግራም የሚላቸውን ለመፈጸም ቃል መግባት —የአሜሪካን ህገር የወደፊት ተስፋ ብሩህ እንዲሆን፣ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል፣ የትምህርት ጥራትና ከፍተኛ ደረጃ ያለው ትምህርት መስጠት ያሻል።

**ከ OCR ጋር ለመገናኘት**

በ የ OCR ዋና ጽሕፈት ቤት ውስጥ ያለው የደንበኛ አገልግሎት ቡድን የ OCRን የሆትላይን (hotline) መስመር ይመልሳል። ደዋዮችም፣ ከፌደራል የሰው ልጅ መብት ሕጎች እስከ የ OCR ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ድረስ ባሉ የተለያዩ አርእስቶችን አስመልክቶ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ፣ እንዲሁም OCR የሚፈጽመውን ሕግን የማስከበር ፕሮግራምን አስመልቶ መረጃ ያገኛሉ።

የሰው ልጅ መብት ቢሮ የሚያስከብራቸውን ሕጎች፣ መብትን በተመለከተ እንዴት አድርገው ቅሬታዎችን እንደሚያቀርቡ ወይም ቴክኒካዊ እርዳታ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ በተመለከተ፣ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ፣ ስቴትዎን ወይም የአሜሪካን ግዛቶችን (U.S. Territory) ከሚያገለግለው የሕግ አስከባሪ ቢሮ ጋር መገናኘት ይችላሉ። ከሕግ አስከባሪው ቢሮ ጋር በዚህ መንገድ መገናኘት ይችላሉ፤ http://www.ed.gov/ocr/contactus.html.

**ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፤**

**የ OCR ሆትላይን፤** 1-800-421-3481፣TDD: 877-521-2172

**ኢ-ሜይል፤** OCR@ed.gov

**ዌብሳይት፤** http://www.ed.gov/ocr